# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

በዲ/ን ቸሬ አበበ

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ ፈቃድ ምን እንደሆነ እንድንረዳ በርሱም እንድንመራ በሰዎች ላይ አድሮ ያናገረው መመሪያችንም እንዲሆን የሰጠው ታላቅ የአምላክ ስጦታ ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተሻለ ሕይወት ለመለወጥ፣ ወደ ቀደመ ጎዳና ለመምራት የሚችል መጽሐፍ ነው። ስለሆነም የመጻሕፍት ሁሉ ራስ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የመጽሐፉን ታላቅነትና ቅድስና ለመግለጥ «*መጻሕፍት አምላካውያት፣ መጻሕፍት ቅዱሳት*» ብላ ትጠራዋለች። ይህም ማለት ቅዱሳን ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ የጻፏቸው የእግዚአብሔርም ቅዱስ ፈቃድ የሚገለጥባቸው፣ የሰው ልጅም በሃይማኖትና በሥነ ምግባር የሚታነጽባቸው የእውነት መፍለቂያ ምንጮች ናቸውና ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ።
ብሉይ ኪዳን ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፈ ሲሆን ሐዲስ ኪዳን ግን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው።

በብሉይ ኪዳን የተጻፈው የማዘጋጃ የተስፋ ቃል ነው፣ በሐዲስ ኪዳን ግን የሆነውን የተደረገውን የሚገልጥ ነው። እነዚህም መጻሕፍት ኪዳናት ይባላሉ። አምላክ በብሉይ የገባውን ቃል ኪዳን በሐዲስ አረጋግጦ እውነተኛ አድርጎ ኪዳኑን አጽንቶ ተገኝቷልና።

እነዚህ ሁለት ኪዳናት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በጥንት ዘመንና በኋላ ዘመን የሰጠውን ተስፋ የሚያረጋግጡ ናቸው። እንዲሁም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ የዋለውን ውለታ የሠራውንም በጎ አድራጎት ሁሉ የሚያስረዱ ናቸው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓላማ

1. የሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወትን የምንማርበትና የምንመራበት መመሪያችን የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ፣መቼና እንዴት በማንስ እንደተፃፈ፣ እውነተኛነቱ ምን ያህል እንደሆነ፣ በውስጡም ምን እንደሚገኝበት ለማወቅ

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው እያንዳንዱ መጽሐፍ የተጻፈበትን ቦታና ቋንቋ፣ የአጻጻፉን ሁኔታ፣ የአተረጓጎሙን ስልት ለማወቅ

3. የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛው ቁጥር /ቀኖና/ በማን፣ መቼና እንዴት እንደተወሰነ የዘመኑ ርቀት፣ የችግሩ ብዛት ሳያጠፋው እንዴት ወደ እኛ እንደደረሰ እንዲሁም ስለአጠናኑና አጠቃቀሙ ለመረዳት

4. በውስጡ የሚገኙትን ታሪክና ሕግ፣ ትምህርትና ትንቢት ሁሉ በትክክል ለመገንዘብ፣ በተገኘውም ግንዛቤ መሠረት ወደ እግዚአብሔር በበለጠ ለመቅረብና በትእዛዙ፣ በፍቅሩና በተስፋው ለመኖር እንድንበቃ ለማድረግ

5. በ1ጴጥ.3.15 ላይ «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ» በተባለው መሠረት ስለመጽሐፍ ቅዱስ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተዘጋጀን እንድንሆን ለማድረግ ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው?

መጽሐፍ የሚለው ቃል ጸሐፈ ጻፈ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ የተጻፈ ወይም ጽሑፍ ማለት ነው። መጽሐፍ ስንል የጽሑፎች የአንድ ላይ ጥራዝ ማለት ነው።

ይህ መጽሐፍ «ቅዱስ» የሚል ቅፅል ተሰጥቶታል፡፡ ቅዱስ የሚለው የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ልዩ፣ ምስጉን፣ንፁሕ፣ክቡር የተቀደሰ ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ ማለት የጽሑፎች አንድ ላይ ጥራዝ ማለት ከሆነና ቅዱስ ማለት ደግሞ ልዩ፣ ክቡር፣ የተቀደሰ ማለት ከሆነ ሁለቱን አንድ ላይ ስናያይዘው «የተቀደሰ፣ የከበረ፣ የተለየ መጽሐፍ ወይም የጽሑፍ ጥራዝ» የሚል ትርጉም እናገኛለን፡፡ ይህ ቀጥተኛ ትርጉሙ ሲሆን ውስጡን በስፋት ስናየው መጽሐፍ ቅዱስጠ

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በሙሉ ያለውን የልቡን ሐሳብ የገለፀበት የምሥጢር መዝገብ ነው፡፡ /አሞ.3.7/፡፡
ከአሁን በፊት በነበሩትና ወደፊት በሚመጡት ዘመናት እግዚአብሔር የፈፀመውንና ሊያደርግ ያሰበውን መለኮታዊ ዕቅድ አካቶ የያዘ ፍፁም ቅዱስ ቃል ነው፡፡
ይዘቱ መለኮታዊ፣ ውበቱ ዘላለማዊ በኃያላን ቃል የማይሻር፣ በአዋቂዎች ዕውቀት የማይሻሻል በጊዜ ሂደት የማይገፋ ሕያው ግንብ ነው፡፡ /ኢሳ.40.8፣ማቴ.5.17፣24. 35፣ ዮሐ.10.35፣ ዕብ.4.12፣1ጴጥ.1.24/፡፡
የእውነት ምንጭ የሆነ በእግዚአብሔር መንፈስና ፈቃድ የተጻፈ፣ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቅ፣ በሥነ ምግባርም በትክክል ይመራበት ዘንድ በቅዱሳን አባቶቻችን በኩል ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡
ስለ እግዚአብሔር ማንነት፣ ስለዓለም አፈጣጠር፣ ስለሰው ውድቀት ብሎም በብዙ መከራ መወጋት፣ ስለማዳኑ ሥራ ከጽንሰት እስከ ዕርገት፣ ስለቤተክርስቲያን መመሥረትና ማደግ፣ በመጨረሻም ስለዳግም ምፅአት የሚናገር በአጠቃላይ ከሌሎች ዓለማውያን መጻሕፍት የተለየ፣ የተከበረና፣ የተቀደሰ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በነቢያት በሐዋርያትና በሰባ ሁለቱ አርድዕት የተጻፉ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንድነት ማለት ነው፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ?

ቅዱስ ማለት ልዩ ክቡር ምስጉን፣ ንጹሕ ማለት ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተሉት ምክንያቶች ቅዱስ ወይም ልዩ ተብሏል፡፡ እነዚህም ጥቂቶቹ-

### 1. ዘመን የማይሽረው በመሆኑ

በብዙ ደራስያን የተጻፉ መጻሕፍት የአንድ ወቅት መወያያ ርእስ እየሆኑ ለታሪክ ወይም ለመረጃ ብቻ የተቀመጡና የሚቀመጡ፣ በዚያውም ሂደቱ እየተለወጠ ሲሄድ የሚሻሻሉ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚያ ሁሉ ተለይቶ ዘመን የማይሽረው፣ ሥርዓተ ማኅበር የማያሻሽለው ወገን፣ጎሣ፣ ጾታ የማይለይ የዘመን ብዛት የማይገታው ዘላለማዊ ነው፡፡ /ኢሳ.40.8፣ 1ጴጥ.1.25፣ ዘዳግ.31.19፣ ገላ.26.29/፡፡

### 2. በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት በመሆኑ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት ባስነሳቸው ቅዱሳን ላይ በጸጋ እያደረ የሚያጽፋቸው እያመለከታቸው የተጻፈ ነው፡፡ /ዘፀ.17.14፣ 2ጴጥ.1.20-21፣ ራዕ.1.11፣ ኤር.3.62/፡፡
በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት ወይም አስገኝ እግዚአብሔር ነው፡፡ /ኢሳ.34.16/፡፡

### 3. በዕድሜው

በዓለም ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት የተጻፈ መጽሐፍ ባለመኖሩ የዕድሜ ባለጠጋነቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

### 4. የሚያነቡትንና የሚሰሙትን ስለሚባርክ

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና ቃሉን በመስማት ቡራኬ ይገኛል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የሚመክር የሚገስጽ የሚያረጋጋ መምህር ነው፡፡ /2ጢሞ.3.17/፡፡

### 5. ዓላማው ቅዱስ ስለሆነና የሚሰሙትን ወደ ቅድስና ስለሚመልስ

«እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ፡፡» እንዲል፡፡ /ዘሌ.19.21፣ 1ጴጥ.1.15/፡፡

### 6. በቅዱሳን አባቶች ስለተጻፈና ስለቅዱሳን የሚናገር በመሆኑ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ስለቅዱሳን መላእክት በአጠቃላይ ስለቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት፣ ንዋያተ ቅድሳት የሚናገር ስለሆነ ቅዱስ ይባላል።

### 7. አስገኚው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ

እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና የእግዚአብሔር የሆነ ሁሉም ቅዱስ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ቅዱስ ነው።

### 8. የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ስላለው ሁኔታ በእርግጠኝነት ስለሚናገር

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ከብዙ ሺሕ ዓመታት በኋላ የተጻፈ ቢሆንም የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት ስለተፈጸመው የሥነ ፍጥረት ሥራ ሲናገር ግን «በይሆናል ወይም ሳይሆን አይቀርም» በማለት በግምት ሳይሆን በእርግጠኝነት ነው። ዘፍ.1.1 እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ ይላል። በተጨማሪም የሰው ልጅ ከተፈጠረ በኋላና ጸሐፊው ከነበረበት ዘመን በፊት ስላለው ሲናገርም እንዲሁ በእርግጠኝነት ነው። ለምሳሌ በዘፍ.12.1 ላይ አብርሃምን እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ አለው ይላል እንጂ እንዲወጣ ሳያደርገው አልቀረም አይልም።

### 9. ወደፊት ስለሚመጣው በእርግጠኝነት ስለሚናገር

መጽሐፍ ቅዱስ ያለፈውን ዘመን በእርግጠኝነት እንደሚናገር ሁሉ ስለሚመጣውም ዘመን ሁኔታ ያለጥርጥር በእርግጠኝነት የሚናገር በመሆኑ ልዩ ነው። ለምሳሌ- «*እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች*» ብሎ ኢሳይያስ በ 7.14 ላይ ሲናገር በወቅቱ ያየ ባይሆንም ነገር ግን ወደፊት እንደሚፈፀም በእግርጠኝነት ትፀንሳለች፣ ትወልዳለች አለ እንጂ ሳትፀንስ፣ ሳትወልድ አትቀርም አላለም። ዳዊትም እንዲሁ እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል አለ እንጂ ሳይመጣ አይቀርም አላለም።/መዝ.49.2/።

ስለዚህ በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከክቡር እግዚአብሔር የተገኘ፣ ስለክቡር እግዚአብሔር የሚናገር ክቡር እግዚአብሔር እርሱ ባከበራቸው ቅዱሳን ሰዎች አድሮ ያስጻፈው ቃል ኪዳኑን ያፀናበት፣ ከሰው ልጅ ጋር የገባበት፣ በቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈና ስለቅዱስ እግዚአብሔር የሚናገር በመሆኑ ቅዱስ ሊባል ችሏል።

## መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?

መጽሐፍ ቅዱስን ቅዱሳን አባቶቻችን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ጻፉት። በእያንዳንዱ ሊቅ፣ ነቢይና ሐዋርያ ላይ አድሮ ያሳሰበ፣ የገለፀ፣ የመራ፣ ያናገረ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። /ዮሐ.14.26፤ 1ቆሮ.12.13/።
ሰዎች ከራሳቸው ልቡና አንቅተው እንደ ልብወለድ እንዳልጻፉ ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነትና ትእዛዝ እንደጻፉ «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ነገር ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት» ሲል ቅዱስ ጴጥሮስ ያስረዳናል። /2ጴጥ.1.20- 21፤ ራእ.1.11/።

እግዚአብሔርም ሙሴን በነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእሥራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው። ይላል /ዘጸ.34.27/።
*«እግዚአብሔር ኢሳይያስን ታላቅ ሠሌዳ ወስደህ ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛም ቸኰለ ብለህ በሰው ፊደል ጻፍበት»* ብሎታል። /ኢሳ.8.1፤ ኤር.36.2/።
ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች በእግዚአብሔር እየታዘዙ የጻፉት ስለሆነ የእግዚአብሔር አሳብ እንጂ የሰው አሳብ አይደለም። /2ነገ.22.8-16፤ ነህ.8.8፤ ኤር.25.1-13 ፤ ኢሳ.34.16/።

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜና ቦታ ከተለያየ የሥራ መስክ በተጠሩ 40 በሚያህሉ ሰዎች እንደተጻፈ ይታመናል። ጸሐፊዎቹ 32ቱ የብሉይ ኪዳን 8ቱ የሐዲስ ኪዳን ናቸው። እነዚህ ቅዱሳን ሰዎች ወደዚህ ግብር ከመጠራታቸው አስቀድሞ የተለያየ ተግባር እንደነበራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ለምሳሌ:-

- ሙሴ እረኛ ነበር። /ዘጸ.3.1/።
- ዳዊትና ሰሎሞን ነገሥታት ናቸው። /ዜና.29.28/።

- ሕዝቅኤል ካህን ነው፡፡ /ሕዝ.1.3/፡፡

- አሞፅ እረኛ ነበር /አሞፅ.1.1/፡፡

- ማቴዎስ ቀራጭ ነበር፡፡ /ማቴ.9.9/፡፡

-ጴጥሮስና ዮሐንስ፣ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፡፡ /ማቴ.4.18-22/፡፡

- ሉቃስ ሐኪም ነው፡፡ /ቆላ.4.4/፡፡

እነዚህ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሁሉም በእግዚአብሔር መንፈስ እየታገዙ ቢጽፉም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች መካከል መጠነኛ ልዩነት አለ፡ ይኸውም: -
1. የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች አምላክ ይወርዳል ይወለዳል እያሉ ሲጽፉ /ኢሳ.7.14/ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፍያን ግን ወረደ፣ ተወለደ፣ ተጠመቀ፣ አስተማረ፣ ሞተ፣ ተነሣ፣ዐረገ ወዘተ እያሉ ጽፈዋል /ሉቃ.2.7፤ ማቴ.3.15፣27.50፣28.6፤ ሉቃ. 24.51/፡፡

2. የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች የጌታን ነገር ለማየት ለመስማት ቢመኙም በዘመናቸው አልሆነላቸውም፡፡ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጻድቃን ሊያዩና ሊሰሙ ወደው ያልሆነላቸውን ሰምተዋል አይተዋል፡፡ /ማቴ.13.16-17/፡፡ ስለሆነም ያዩትን የሰሙትን የዳሰሱትን ተናግረዋል ጽፈዋል፡፡ /1ዮሐ.1.3/፡፡ ያየነውን የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን እያሉ አስረድተዋል፡፡

ይህም ቅዱሳን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል የሚመሰልባቸው ነገሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ በእሳት፣ በመዶሻ /ኤር.23.29/፣ በብርሃን /መዝ.118.105/፣ በምግብ /ኤር.15.18 ፤ መዝ.118.105/፣ በወተት /1ጴጥ. 2.3፤ ዕብ.12.13፤ 1ቆሮ.3.12/፣ በሰይፍ /ኤፌ.6.17፣ ዕብ.4.12/ በዘር /ማቴ.1.1- 3/ በንፁህ ወይም በተጣራ ብር /መዝ.11.6/ በመስታወት /ያዕ.1.23-25/ ወዘተ ይመሰላል፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ከብዙ ወርቅና ብር ይልቃል /መዝ.116.72/፣ እንደማር ይጣፍጣል /ሕዝ.3.1-3፤ ራዕ.10.8-16/ ዳኛ ነው ይፈርዳል፡፡ /ዮሐ.12.48/ ርስት መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳል /ሐዋ.20.32/፤ የመዳን ቃል ነው፡፡ /ሐዋ.13.26/፡፡

### መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ያስፈለገበት ዐበይት ምክንያቶች

1. የሰው ልጅ አስቦ ሊደርስ የማይችለውን ነገር ለማሳወቅ

2. ያለ ስህተት ያለ ልዩነት እንዲጻፍ ለማድረግ

3. አንድ ዓይነት የሃይማኖት፣ የሥነምግባር ሥርዓት እንዲኖረን አዘጋጅቶ ሊሰጠን ስለፈቀደ

4. እግዚአብሔር እንዲጻፉ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ሳይጻፉ እንዳይቀሩና የማያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ደግሞ እንዳይጻፉ አንድን ጉዳይ የመምረጥና ሌላውን ጉዳይ የመተው ችሎታ እንዲኖራቸው መንፈስ ቅዱስ ሕሊናቸውን አብርቶላቸው የጻፉ መሆናቸው ነው፡፡

## ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ ጸሐፊዎችን የረዳው፡

1. እንደሙሴ ቃል በቃል በማነጋገር /ዘኁ.12.4-8/፡፡
2. እንደዮሴፍ በሕልም በመግለፅ /ዘፍ.37.5/
3. እንደነቢያት በትንቢትና በራእይ በመግለጽ /ዘኁ.12.6፣ ዮሐ.ራዕ.1.10-11/፡፡

የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን የእግዚአብሔር መንፈስ ከስህተት የሚጠብቃቸው መሆኑ ቢታወቅም በራሳቸው አስተሳሰብ ምንም ለማድረግ የማይችሉና ነፃ ፈቃድ የሌላቸው አይደሉም፡፡ ነገር ግን ተናጋሪና ሕያው የሆነ ነፃ ፍላጎት ያላቸው ቢሆኑም በእግዚአብሔር ፈቃድና በፍላጎቱ መሠረት የሚሠሩ መሆናቸውን የሚያምኑ ናቸው፡፡ ይህም ማለት የመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጸሐፊውን የአጻጻፍ ዘዴ አይለውጠውም ማለት ነው፡፡ ስህተት እንዳይፈጸሙ ጥበቃ የሚያደርግላቸው መሆኑ ቢታወቅም እያንዳንዱ ጸሐፊ የራሱ በሆነ የአጻጻፍ ዘይቤ ጻፈ እንጂ የሁሉም ጸሐፍያን አጻጻፍ አንድ ዓይነት አይደለም፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዓላማ

1. የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት የፈጠረ እግዚአብሔር እንደሆነ ዓለምን ከመፍጠሩ በፊትም ሆነ በኋላ በክብር፣ በአንድነት፣ በሦስትነት እንዳለ ለመግለጥ፡፡ /ዘፍ.1.26፤ ማቴ.28.19፣11.7፤ ዮሐ.1.1-4/፡፡

2. እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ለማስረዳትና እሱን ብቻ እንድናመልክ ለማስተማር፡፡ /ዘጸ.10.2-6/፡፡

3. የእግዚአብሔር ባሕርይና ዘላለማዊ ፈቃድ ምን እንደሆነ አውቀን እንደፈቃዱ እንድንመራ ለማድረግ፡፡ /ሮሜ.15.4/፡፡

4. ሥጋን ለብሶ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር እንደሆነ አምነን በስሙም ዘላለማዊ ሕይወትን እናገኝ ዘንድ፡፡ /ዮሐ.20.30፤ ዮሐ.5.13/፡፡

5. እግዚአብሔር ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኞችን እንደማይጠላ፣ በንስሐ ወደ እርሱ እንድንመለስ እንደሚፈልግና ከተመለስን ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃን ለማስረዳት፡፡

6. በተዋሕዶ ዓለምን የማዳኑን ድንቅ ሥራ ለማሳወቅና ለማስገንዘብ

7. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር እንደዐረገ በክብር ለፍርድና ይህን ዓለም ለማሳለፍ እንደሚመጣ አውቀን ተዘጋጅተን እንድንኖር ለማሳሰብ ነው፡፡ /ማቴ. 24 እና 25/፡፡

### በአጠቃላይ ይህ ቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው: -

ሀ. ለትምህርታችን ነው «በመጽናት መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና» /ሮሜ.15.4/፡፡

ለ. ሊገስጸን ነው «ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገስጸን ተጻፈ» /1ቆሮ.10.11/፡፡

ሐ. የዘላለም ሕይወት እንዴት እንደምናገኝ ሊያሳየን ተጻፈ «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ. . . ጽፌላችኋለሁ፡፡» /1ዮሐ.5.13/፡፡

መ. በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር ወይም መመላለስ እንዳለብን ሊያስተምረን ነው «በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍለሃለሁ፡፡» /1ጢሞ.3.15/፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅም

### 1. የበለጠ እግዚአብሔርን ለማወቅ
መጽሐፍ ቅዱስ የአእምሮን ዕውቀትን ለማዳበር ብቻ የሚጠና አይደለም፡፡ ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉትን ረቂቅ የእግዚአብሔር ሥራዎች የምንረዳበት የምናውቅበት ነው፡፡ «እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት ያላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡» /ዮሐ.5.39/፡፡

### 2. ለመቀደስ
በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የሚያነቡትን የሚያጠኑትን የሚጸልዩትን ይቀድሳል፡፡«በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው፡፡» /ዮሐ.17.17 ፤ ኤፌ.5.26/

### 3. ክፉንና በጎን ለይቶ ለማወቅ
«ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡» /መዝ.118.105/፡፡

### 4. ማስተዋልን ለማግኘት
«ትእዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ ምስክርህ ትዝታዬ ነውና ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አስተዋልሁ ትእዛዝህን ፈልጌአለሁና ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋልሁ፡፡» /መዝ.118.100/

### 5. ቃሉን በመጠበቅ በትክክለኛው መንገድ ለመራመድ
«ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነፃል ቃልህን በመጠበቅ ነው።» /መዝ.118.9/

### 6. እግዚአብሔርን ከመበደል ለመጠበቅ
«አንተን እንዳልበድል ቃልህን ሰወርሁ።»/መዝ.118.11/።

### 7. በሥራ መከናወንን ለማግኘት
«የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል። ይከናወንልሃልም።» /ኢያ.1.8/።

### 8. ለበጎ ሥራ ለመታጠቅ
«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» /2ጢሞ.3.16-17/።

### 9. ከኃጢአት ነጻ ለመሆንና በረከትንም ለማግኘት
«ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፣ በሥራው የተባረከ ይሆናል። /ያዕ.1.25/።

### 10. እውነትን ለማወቅ
እምነትህ በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ለአንተ ዛሬ እነሆ አስታወቅሁህ። የእውነትን ቃል ርግጥነት አስታውቅህ ዘንድ፣ ለሚጠይቅህም እውነትን ቃል መመለስ ይቻልህ ዘንድ፣ በምክርና በእውቀት የከበረን ነገር አልጻፍሁልህምን? /ምሳ. 22.19-20/።

### 11. እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ቃል የገባልንን መንፈሳዊ ርስት ለመቀበል
« አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስት ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።» /ሐዋ.20.32/።

### 12. መንፈሳዊ ውጊያን ለመዋጋት
«. . . የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። » /ኤፌ. 6.10-18/።

## መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዘመን

በቤተክርስቲያን የብሉያትና የሐዲሳት መምህራን አስተምህሮት ሁለቱም ኪዳናት የተጻፉበት ጊዜና ወቅት የተረዳ ነው። ይኸውም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አስቀድሞ የተጻፈው መጽሐፈ ሄኖክ ነው። መጽሐፈ ሄኖክ ዓለም ከተፈጠረ በ1486 ቅ.ል.ክ ዘመን ተጽፏል። ከዚህም ቀጥሎ እስራኤል በግብጽ ሳሉ በፈርኦን ዘመን መጽሐፈ ኢዮብ ተጽፏል።

በ3843 ቅ.ል.ክ እስራኤል ከግብጽ ወጡ፣ በዚህ ጊዜ መጻሕፈ ኦሪት ተጻፈ።
በ4407 ቅ.ል.ክ ሳኦል ሞቶ ዳዊት ነገሠ። በዚህ ጊዜ የዳዊት መዝሙር ተጻፈ።

በ4481 ቅ.ል.ክ ዳዊት ሞቶ ሰሎሞን ነገሠ ሰሎሞን በነገሠ በዐራት ዓመት /1ነገ.10.1/ የኢትዮጵያ ንግሥት በጥሮዋ የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብ አይቶ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ንግሥት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማወቅ ኢየሩሳሌም ስለወረደች «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር»ተብሎ የተነገረልን ትንቢት ተጀመረልን። መዝ.87.። የሔደችበትም ምክንያት አምለኮተ እግዚአብሔርን ስትፈልግ እንደሆነ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል «ንግሥተ አዜብ ከዚህ ሕዝብ ጋር በፍርድ ቀን ትነሣለች ትፋረዳቸዋለችም ከምድር ዳር መጥታለችና የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ሔደች።» በማለት ተገልጿል። /ማቴ.12.32/። ሰሎሞንም እንደ መንግሥቱ ደግነት አክብሮ ተቀበላት ከዚህ በኋላ የሔደችበት ምክንያት አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትሻ ነውና አምልኮተ እግዚአብሔርን አምልቶ አስፍቶ የወደደችውን ሁሉ ነግሯታል። /1ነገ.10.13/።

እርሷም አምልኮቱን ተረድታ « በዘርእከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር፣ የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ።» ብሎ ጌታ ለአብርሃም የተናገረው ተስፋ ሊፈጸም ምኒሊክን ከሰሎሞን ጸንሳ ወደ ሀገሯ ተመለሰች። ምኒልክም ተወልዶ 22 ዓመት ሲሆነው ወደ አባቱ ወደ ሰሎሞን ሄደ ሰሎሞንም ልጁ

መሆኑን ለእስራኤል አስታወቀ፤ እስራኤልም ልጁ መሆኑን ካወቁ በኋላ ለሁለት ነገሥታት መገዛት አይቻለንምና በእናቱ ሀገር አንግሠህ ስደደው አሉት። እርሱም የበኸር ልጅህን ስደድ ካላችሁኝ እናንተም የበኸር የበኸር ልጃችሁን አምጡ አላቸው። አምጥተውም ሰጡት።

ከዚህ በኋላ ሥርዓተ መንግሥት አድርሶ ምኒልክን አንግሦ ከሄኖክ አንስቶ እርሱ እስከጻፋቸው ድረስ ያሉትን መጻሕፍት ሰብስቦ እነዚህን መጻሕፍት ተርጉመው የሚያስተምሩ 318 ሌዋውያን /ካህናትን/ ጨምሮ ልኳል። እነርሱም መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተርጉመው አስተምረዋል። ሀገረ ብሉይ ወሐዲስ የተባለች ኢትዮጵያም የቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤት እንድትሆን ካስቻሏት አንዱ ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን /ቅዱሳት መጻሕፍት/ ደራስያን ጋር ያላት ግንኙነት ከፍተኛ መሆኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ አስቀድሞ ከኢየሩሳሌም ጋር የነበራት የታሪክ ትስስር ነው። ስለዚህም በብሉይ ኪዳን ከሔኖክ፣ከሙሴ፣ ከኤርምያስ፣ ወዘተ አበው ነቢያት፤ በሐዲስ ኪዳን በኩልም በዘመኑ ከቅዱስ ማቴዎስ፣ ከፊሊጶስ፣ሌሎችም ተጠቃሾች ናቸው። /መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ትርጓሜ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም/

## መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቦታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሁሉም በአንድ ወቅትና አንድ ላይ ተሰብስበው እንዳይደለ ገልጽ ነው። በዚህም መሠረት

> የሙሴ መጻሕፍት /ዘፍጥረት፣ዘጸአት፣ዘሌዋውያን፣ዘኁልቁ፣ ዘዳግም፣/ በሲና በረሃ፣
> መጽሐፈ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ነገሥት፣ዜና መዋዕልጠበምድረ ከነዓን / በከነዓን ምድር/
> መጽሐፈ አስቴር፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ዮዲት በፋርስ ባቢሎን በምርኮ ሳሉ
> የማርቆስ ወንጌል በግብጽ
> የማቴዎስ ወንጌል በፍልስጥኤም.
> የቅዱስ ጳውሎስና የዮሐንስ መልእክታት በታናሽ እስያ

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ በመካከለኛው የምሥራቅ ክፍለ ዓለም የተጻፈ ነው፡

## መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለመጀመሪያ ጊዜ በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆን ከነዚያም የተወሰኑት ማለት መጽሐፈ ዕዝራና ዳንኤል በአራማይክ እንደተጻፉ ይነገራል።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በግሪክ /ጽርዕ/ ቋንቋ ነው። ሆኖም ፖፒያስ የተባለው ሊቅ ማቴዎስ ወንጌልን በመጀመሪያ የላከው ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ለተቀበሉት ስለነበር በዕብራይስጥ እንደጻፈው ይነገራል። ከጊዜ በኋላ ግን ከዕብራይስጥ በዚያ ዘመን በጊዜው ብዙው ሕዝብ ወደሚረዳው ቋንቋ ወደ ግሪክኛ ተተርጉሟል። በየቦታው ተበትነው /ተወስደው/ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ቋንቋቸውን ረስተው በዚያን ጊዜ የዓለም አቀፍ/ፅነተጽረነቷተፀጻነቷለ/ ቋንቋ በነበረው በግሪክኛ ይናገሩ ስለነበር በጥሊሞስ የሚባል የግብጽ ንጉሥ ከ294-247ቅ.ል.ክ ብሉይ ኪዳንን ለመጀመሪያ ጊዜ በሰባ ሊቃናት /ስጽፐተጭቷ1ፀነተ/ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ አስተረጎመላቸው። ይህ ትርጉም መጽሐፍ በተርጓሚዎቹ ቁጥር የሰባው ሊቃናት ትርጉም ወይም ሴፕቱ ኢጅንት ተብሏል።

ከዚህ በኋላ የብሉይንና የሐዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ክርስቲያኖች አንብበው በውስጣቸው ባሉት መንፈሳዊ ትምህርቶች፣ ምክሮችና ተግሳጾች በመጠቀም ድኅነትን እንዲያገኙ ታስቦ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ለምሳሌ ከክርስቶስ ልደት በፊት በንግሥተ አዜብ ወይም ንግሥት ሳባና በልጇ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት ሰሎሞን የጻፋቸውንና ከዚያ በፊት የተጻፉ መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በግእዝ ተተርጉመዋል። በአይሹር ወይም አይዙር መንግሥትም የነቢያት መጻሕፍት ወደ ሀገራችን ገብተው ተተርጉመዋል።

ምንም እንኳ የትርጉሙ ሁኔታ ቢለያይም ከክርስቶስ ልደት በኋላም መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሀገሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ለምሳሌ-

> በግብጽ ወደ ቅብጥ ቋንቋ
> በአርማንያም ቅዱስ ሜስሮን እና ቅዱስ ሳሃክ /ከ3ኛው እስከ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ አርመን ቋንቋ ተረጎሙ

ቅዱስ ሄሮኒመስም ጀሮም በ4ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ ጥንታውያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልባጮች በማስተያየት ቢብልያ ቩልጋታ የሚባለውን የሮማይስጥ /የላቲን/ ትርጉም አዘጋጀ፡፡

በኢትዮጵያም በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጡ ተሰዓቱ/ዘጠኙ/ ቅዱሳን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ እንዲተረጎሙ አደረጉ፡፡ ከእነሱም ዘመን ቀደም ብሎ አንዳንድ መጻሕፍት በእነ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ፍሬምናጦስ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተተርጉመዋል፡፡

በአውሮ ማርቲን ሉተር /1483-1546 እ.ኤ.አ/ ወደ ጀርመንኛ ተረጎመው

ኤራስሙስ/1466-1536/ አዲስ ኪዳንን ከጥንታውያን ጽሑፎች ጋር አስተያይቶና አቃንቶ ወደ ላቲን ተረጎመው፡፡

ዊክሊፍ /1329-1384/ እና ቲንዴል /1494-1536/ ወደ እንግሊዝኛ በ1525 ዓ.ም ተርጉመዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን በኢትዮጵያ በነጠላ ትርጓሜ ወደ አማርኛ የተረጎመው አብርሃም /አባ ሮሜ/ የሚባል መነኩሴ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ያስረዳሉ፡፡ ይህም ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1816 ዓ.ም አራቱ ወንጌላት በ1821 ዓ.ም ሐዲስ ኪዳን በ1832 ዓ.ም ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ወጣ፡፡

የዕብራይስጥና የግሪክ ቋንቋ የሚያውቁ አንዳንድ የውጭ ሀገር ዜጎች /ለምሳሌ ማርቲን ፍላድ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር ትርጉሙን ካሻሻሉት በኋላ በ1878 ዓ.ም እንደገና ታርሞ ታተመ፡፡ ከኢጣልያ ወረራ በኋላ የቀድሞው ትርጉም እንዲታረም ስለታሰበ ብዙ ሊቃውንት ከደከሙበት በኋላ በ1953 ዓ.ም አዲስ ትርጉም ታተመ፡፡ ዛሬ በብዛት በሰው እጅ የሚገኘው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነው፡፡

አለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ትግርኛ፣ የወለጋው ተወላጅ አኔሴሞስ ነሲብም ወደ ኦሮምኛ ተርጉመውታል፡፡

## የ፹፩ሥራው ቅዱሳት መጻሕፍት ስያሜ አሰጣጥ

ቅዱሳት መጻሕፍት በጸሐፊዎች፣በይዘታቸውና በከተሞች ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለምሳሌ

### ሀ. በጸሐፊው ስም የተሰየሙ

መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል፣ መጽሐፈ ዕዝራ፣ መጽሐፈ ነህምያ፣ ወንጌላት፣ የቅዱስ ጴጥሮስ፣የቅዱስ ዮሐንስ፣ የቅዱስ ያዕቆብ፣ የቅዱስ ይሁዳ መልእክታት

### ለ. ከይዘታቸው በመነሳት የተሰጣቸው

ለምሳለ@- ኦሪት ዘፍጥረት የተጻፈው በሙሴ ሲሆን የሚጠራው ግን «ኦሪት ዘፍጥረት» ተብሎ ነው፡፡ ይህም የሥነ ፍጥረትን ነገር የሚናገር በመሆኑ የተሰጠው ስም ነው፡፡ ኦሪት ዘጸአት የሚለው መጠሪያም ከመጽሐፉ ይዘት በመነሳት የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ዘጸአት ቃሉ ግእዝ ሲሆን ትርጉሙ መውጣት ማለት ነው፡፡ የእሥራኤልን ከግብጽ መውጣትን በስፋት ስለሚተርክ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ኦሪት ዘሌዋውያን በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያት የአሮን ልጆች ሌዋውያን በእግዚአብሔር ዘንድ ለክህነት የተመረጡ ነበሩ፡፡ ይህ መጽሐፍ ደግሞ ስለ ካህናት አሿሿም እና ሊፈጽሟቸው ስለሚገባቸው ሕግጋት የተጻፈበት በመሆኑ ኦሪት ዘሌዋውያን ተብሏል፡፡ ኦሪት ዘኁልቁ የሚለው የግእዝ ቃል ቆጠራን የሚያመለክት ሲሆን መጽሐፉም ስለ እስራኤል ልጆች መቆጠር ስለሚተርክ በይዘቱ ምክንያት ስያሜው ተሰጥቶታል፡፡

መጽሐፈ መሳፍንት የሚለውም በእስራኤል ስለተነሡት መሳፍንት የሚናገር ነው፡፡ መጽሐፈ ነገሥት ስለ ነገሥታት ስለሚናገር፣ መጽሐፈ ምሳሌ በምሳሌያዊ ንግግር ስለተጻፈ፣ መጽሐፈ ዜና መዋዕል በወቅቱ ስለነበሩት ነገሥታትና ሕዝቦች ስለሚተርክ፣ መጽሐፈ ኲፋሌ ከኦሪት የተከፈለ ስለሆነ፣ የሐዋርያት ሥራ በውስጡ የሐዋርያትን ገድል ስለሚናገር፡፡ መጽሐፈ አስቴር ደግሞ ጸሐፊው የአስቴር አጎት መርዶክዮስ ሲሆን የሚጠራው ግን በባለታሪኳ በአስቴር ነው፡፡

### ሐ. በጸሐፊው እና በይዘታቸው /በሁለቱም/ የሚጠሩ

ለምሳሌ- «መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን» ጸሐፊውንና ይዘቱን የሚያመለክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ መኃልየ መኃልይ ማለት የመዝሙራት ሁሉ መዝሙር ማለት ሲሆን በይዘቱ ክርስቶስን እመቤታችንን እና ቤተክርስቲያንን የሚያወድስ ስለሆነ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ዘሰሎሞን ሲል ደግሞ መጽሐፉ የሰሎሞን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ ወንጌል ዘማቴዎስ፣ መጽሐፈ ራእዩ ለዮሐንስ የሚሉትን ብንመለከት

ጸሐፊያቸውንም የመጻሕፍቱንም ይዘት ማወቅ ያስችላል:: የማቴዎስ ወንጌል ሲል ጸሐፊው ማቴዎስ መሆኑን መጽሐፉም ስለ ወንጌል ሥራ /አገልግሎት/ የሚያስረዳ መሆኑን ያሳያል:: የዮሐንስ ራእይም ጸሐፊው ዮሐንስ እንደሆነና በይዘቱ ራእይ መሆኑን ያስረዳል::

መ. በከተማ ስም የተጠሩ

ከአሥራ አራቱ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ዘጠኙ በተላኩላቸው ከተሞች የተጠሩ ናቸው:: እነዚህም ሮሜ፣ ቆሮንቶስ፣ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ቆላስይስና ተሰሎንቄ ናቸው::

ሠ. በተላኩላቸው ሰዎች ስም የተጠሩ

ጢሞቴዎስ፣ ቲቶና ፊልሞና ሲሆኑ ዕብራውያንም መልእክቱ ከተላከላቸው ወገኖች ከተጠሩት መጻሕፍት አንዱ ነው::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ጊዜው በጣም ሩቅ ሲሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ እስከዚህ ሊደርስ የቻለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው::

1. በቤተ መቅደስ በክብር ያስቀምጡት ስለነበር:: /ዘዳግ.32.44-47 ፣ 2ነገ.22.8፣ ዘዳግ.31.24፣ ሉቃ.4.16-20/::
2. የቀድሞ ጸሐፊዎች በዓለት፣በሰሌዳ ላይ በጡብና በብራና በክርታስም ጽፈው ያስቀምጡ ስለነበር:: /ኢዮ.19.23-24፣ኢሳ.8.1፤ 30.8፣ ሕዝ.4.1፣ ኤር.36. 2-32/::

3. አረማውያን ነገሥታት ቤተ መቅደስንና ቤተክርስቲያን ሲያወድሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያቃጥሉ አባቶቻችን መጻሕፍቱን ይዘው በመሰደድ በየዋሻው ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር ሕይወታቸውን ሰውተው ለተተኪው ትውልድ ታላቁን ሀብት አቆይተዋል::

4. የእግዚአብሔር ቃል ዘለዓለማዊ ስለሆነ:: /ኢሳ.40.8፣ዕብ.4.12፣1ጴጥ.1.24/::

## የዐሥራው ቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ አሁኑ በአንድ ላይ ከመጀመሪያ ጀምሮ የተጠረዘ ስላልነበረ በውስጡ ያሉት የመጻሕፍቱ ቁጥር ወይም ብዛት ያከራክር ነበር:: ሰባው ሊቃናት በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ የተረጎሙት 46ቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነበር:: ከጊዜ በኋላ አይሁድ ግን 39ኙን ብቻ ተቀብለው ሌሎችን ተውአቸው:: በዚህ መሠረት ቅዱስ ጀሮም የተባለው የላቲን ሀገር ሰው ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ላቲን ሲተረጉም 39ኙን ብቻ አገኘ:: የተቀሩትን ግን ከሰባው ሊቃውንት ትርጉም መጽሐፍ ወስዶ በዕብራይስጥ አግኝቶ ከተረጎማቸው መጻሕፍት ጋር አብሮ አንድ አድርጎ ያዛቸው:: ከዕብራይስጥ የተረጎማቸውን ቀኖና ብሎ ሲሰይማቸውና ሲቀበላቸው የቀሩትን አፖክሪፋ ብሎአቸዋል:: የተሠወሩ ወይም ኅቡዕ ሲላቸው ነው:: ከቀኖናው ውጭ የሆኑ ለማለት ነው::

ክርስቲያኖች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሚያነቡት የተለየ ክርስቲያናዊ ጽሑፍ ባለመኖሩ ይጠቀሙበት የነበረው ብሉይ ኪዳን ነው:: ይህ ብሉይ ኪዳን ቀደም ብሎ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ ተተርጉሞ ተባዝቶም ስለተገኘ ክርስቲያኖች ሁሉ በዚህ ይጠቀሙ ነበር::

ይህም ሊሆን የቻለው-

1. በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ወደ ክርስትና ይመጡ ከነበሩ ሕዝቦች መካከል የሚበዙት አይሁድ ስለነበሩ

2. በጽሑፍ ውሎ የተገኘው መጽሐፍ ይህ ብሉይ ኪዳን ብቻ በመሆኑ ክርስቲያኑም አይሁድም ይጠ ቀሙበት ነበርና ነው::
እንደሚታወቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ እንጂ አልፃፈም፣ ሐዋርያትም በቃል ብቻ ተማሩ፣ በቃልም ብቻ አስተማሩ እንጂ በመጀመሪያው ጊዜ አልፃፉም ነበር:: ስለዚህ ሁሉም በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መጠቀም ግድ ሆነ::

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ግን የጌታችን ቃላት ናቸው የሚባሉትን እንደ ጥቅስ እያደረጉ በመጽሐፍ ማስፈር ጀመሩ። በዚህ መልክ በየቦታው በየቤተክርስቲያኑ አንዱ በማብዛት ሌላውም በማሳነስ ይጽፉ ጀመር። ቀስ በቀስ እነዚህን የተለያዩ ጽሑፎች መሰብሰብ ተጀመረ፤ ማለት ቤተክርስቲያን አንዲት እንደመሆኗ መጠን በአንድም መንፈስ ስለምትመራ የተለያዩትን ጽሑፎች ሁሉ ማገናኘት መሰብሰብ ተጀመረ። እነዚህም ጽሑፎች ለወንጌል ጽሕፈት መነሻ ሆኑ።

በዚህ መልክ የተሰበሰቡ ጽሑፎች ሁሉ በየሳምንቱ እሑድ በቤተክርስቲያን መነበብ ጀመሩ። እነዚህም ቀስ በቀስ ወደ ወንጌል ጽሑፍ አመሩና ቃላቱ የክርስቲያን መመሪያ የጌታ ቃል ለሕዝብ የምሥራች/ወንጌል/ ሆነው ተፃፉ። መልእክታትም የራሳቸው ታሪክ አላቸው። እነዚህም ጽሑፎች በየሳምንቱ እሑድ በየቤተክርስቲያኑ በመነበባቸው በምእመናን ዘንድ የታወቁ ሆኑ።

ይህቺን አጋጣሚ በመጠቀም በዚያን ጊዜ የነበሩ ከሀዲዎች በሐዋርያት ስም የክህደት ትምህርታቸውን ያዘሉ የወንጌልና መልእክታት እየፃፉ በምእመናን መካከልና በቤተክርስቲያን ውስጥ ማሰራጨት ጀመሩ። ስለዚህም እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለመለየት ብዙ ሰዎችን ግራ አጋብቶ ነበር።

ይሁን እንጂ ቅድስት ቤተክርስቲያን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በታላቅ ጥንቃቄ መርምራ ከከሐዲዎች መጻሕፍት ለይታ 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተቀበለች። በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት ቁጥር 27 መሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው የእስክንድርያው ትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ በ367 ዓ.ም የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ለአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በጻፈላቸው መልእክት ውስጥ ነው። በ397ዓ.ም በቅርጣግና /ካርቴጅ/ ላይ በተደረገው ሲኖዶስ 27ቱን መጻሕፍት አጸደቀ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን «ሃይማኖት ያለ ምግባር በራሱ የሞተ ነው» እንዲል/ያዕ.2.17/ ከእነዚህ 27 የሃይማኖት/ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሌሎች ተጨማሪ ስምንት የሥርዓት መጻሕፍትን ቆጥራ ሰፍራ በሲኖዶስ ወስና ትቀበላለች። እነዚህ ስምንት የሥርዓት መጻሕፍት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ጌታ የሠራውን የሃይማኖትና የሥርዓት አጠቃላይ ትምህርት የሚያዝ ነው። ስለሆነም መጻሕፍቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አጠቃላይ ቁጥር 35 ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮ በሚል በእንግሊዝኛና በአማርኛ የታተመ መጽሐፍ ተገልጾ ይገኛል።

**ቅዱሳን አባቶች እውነተኞች መጻሕፍትን ከሐሰተኞች መጻሕፍት የለዩበት ዘዴ**

1. ሐዋርያዊ ጽሑፍ መሆኑ ሲታወቅ- ይህም ማለት በመጀመሪያ የተቀበሉት በሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት በነበራቸውና በታወቁ ሰዎች የተጻፉትን በመለየት ነበር። ለምሳሌ- የማርቆስን ወንጌል ለመቀበል ቅዱስ ማርቆስ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር መሆኑ ታውቆ፣ ከሐዋርያትም ጋር አብሮ ሲወጣ ሲወርድ የነበረ ስለሆነ፣ የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን ለመቀበል ደግሞ ሉቃስ ከጳዉሎስ ጋር ሲወጣና ሲወርድ መኖሩ ስለታወቀ ነው።

2. የመጽሐፉ መንፈሳዊነት ሲታወቅ- ለሰው መንፈሳዊ ሕይወት የሚጠቅም የሚስማማ ሲሆን ማለት በመላ ይዘቱ በእግዚአብሔር መንፈስ መጻፉን የሚያመለክት ሲሆን። ይህም ሲባል መጽሐፉ የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት የማያፋልስ መሆኑ ሲታወቅ ተቀባይነትን ያገኛል።

3. ከቤተክርስቲያን ግምጃ ቤት መገኘቱ ሲታወቅና ተቀባይነት ሲያገኝ- በጊዜው የነበሩ ሐዋርያት የፃፏቸው መጻሕፍት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲውሉ ተብለው በቤተክርስቲያን ግምጃ ቤቶች ይቀመጡ ስለነበር እውነተኛነቱ እንዲታወቅ ከቤተክርስቲያን ግምጃ ቤት መገኘት አለበት። በተጨማሪም በዓለም የምትገኘው በቦታ ተከፋፍላ በእምነትና በትምህርት አንድ የሆነችው ቤተክርስቲያን ያለመለያየት ቀኖና የሆነውን በየቦታው ተስማምታ ስትቀበለው።

4. ቅዱሳኑ ልዑል እግዚአብሔርን በማመን የመጻሕፍቱ ተአምራት ማድረግ ሲረጋገጥ- ቅዱሳን አባቶቻችን ከሌላዎቹ ተቀባይነት ከሌላቸው መጻሕፍቱን የሚለዩበት መንገድ አንዱ ተአምራት ማድረጋቸውንና አለማድረጋቸውን በማረጋገጥ ነበር። ይኸውም መጻሕፍቱ ከእሳት ሲጣሉ እሳቱ ሳያቃጥላቸው ከቀረ፤ ከውኃ ውስጥ ሲጨምሯቸው ውኃውም ሳያበላሻቸው ሲቀር፤ የተለያዩ በሽተኞችን ሲፈውሱ፤ ከሙታን ዘንድ ሲያስቀምጧቸው ሙታንን ሲያስነሱ ወይም ሌሎች ተአምራት ሲያደርጉ መጻሕፍቱ ተቀባይነት ይኖራቸው ነበር። በዚህም መንገድ ለይተዋቸዋል።

ምንም እንኳ እነሱ ባወጡት መሥፈርት መሠረት መጻሕፍቱን እየጣሉ እየተቀበሉ ቢመጡም ለማንኛውም ነገር መራጭ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎቹ አድሮ አብሮ ከእነርሱ ጋር መርጧል መልካሙን እንዲመርጡም ልቦና ሰጥቶአቸዋል::

በዚህ መሠረት አንዳንድ በየጊዜው ጥናት ያላደረጉትና ያልመረመሩ አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ብለው ተቀብለዋቸው የነበሩትን የሐሰት ጽሑፎች እንደያዙ ቢቆዩም የበለጠው ክፍል አውጥቶ ጥሎአቸዋል:: 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ብቻ ተቀብሏቸው:: ከዚህ በኋላ ቤተክርስቲያን በጥብቅ መርምራ ንጹሕ ሆኖ ያገኘችው ይኸው ብቻ ስለሆነ ቅዱስ ብላ ቅዱስም አድርጋ ይዛዋለች::

እነዚህን 3ቱን የመለያ ዘዴዎች ቤተክርስቲያን በአንድ ጊዜ የወሰነችው አልነበረም በአንድ ጊዜ የሆነና የተፈፀመም ነገር አልነበረም፣ የዚህ እውነት እስኪወጣ ግን ብዙ ጊዜ ፈጅቷል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሐዶ ቤተክርስቲያን 81 መጻሕፍትን ትቀበላለች:: 46ቱ የብሉይ ኪዳን ሲሆኑ 35ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው:: ከ35ቱ፣ 27ቱ የቀኖና ሲሆኑ 8ቱ የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው::

በአይሁድ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 24 ሲሆን በግሪክ ኦርቶዶክስ 76 በካቶሊክ 73 በፕሮቶስታንት 66 ነው::
እነዚህ በእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ከመጀመሪያ እንደ አሁኑ በምዕራፍና በቁጥር የተከፋፈሉ አልነበሩም:: ወይንም መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ቅዱሳን ሰዎች እንደ አሁኑ በምዕራፍና በቁጥር ከፋፍለው አልፃፏቸውም:: ነገር ግን በ1228 ዓ.ም በእንግሊዝ ሀገር በምዕራፍ፣በ1551 ዓ.ም በፈረንሳይ ሀገር በቁጥር ተከፈለ::

## የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈልና ዝርዝር

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል:: እነርሱም ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን በመባል ይታወቃሉ::
ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሙሴ አማካኝነት የሰጣቸው ቃል ኪዳን ነው:: ብሉይ ማለት የጥንት፣የቆየ ማለት ሲሆን ኪዳን ማለት ውል፣ ስምምነት፣ መሐላ ማለት ነው:: በኋላ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን ዘመን ሁሉ እንደ አሮጌ በመቁጠር ከዚያ በፊት የተፃፉትን ብሉያት ብሏቸዋል:: «ብሉይ» ወይም አሮጌ ሲል ግን ማርጀትን ወይም ማፍጀትን ሳይሆን የዘመንን ርዝማኔ የሚያስረዳ ነው:: ምክንያቱም በማቴ.24.36 እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ቃል ዘመናትን አሳልፎ ለዘለዓለም የሚኖር ሁልጊዜ የማይሻር የማያልፍ ነውና::

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ድኅነት ሲል የሰጠውን ታላቁን ተስፋ ቀስ በቀስ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ ገለጸው:: ቤተ እስራኤልም ተስፋቸውን ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ አዘጋጀ:: በሲና ተራራ ቃል ኪዳኑን በመስጠት የተስፋውን ቃል አረጋገጠ:: እነርሱ ሕጉንና ሥርዓቱን ሊጠብቁ፣ እርሱ ደግሞ አምላክ ሊሆናቸው ተስፋውንም ሊሰጣቸው ቃል ገባላቸው:: /ዘጸ.24.1-11/::

ሁለተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሐዲስ ኪዳን ሲሆን ትርጉሙም አዲስ ውል፣ ስምምነት ማለት ነው:: ሐዲስ ኪዳን የተባለበትም ምክንያት በኤር.31.31-34 ላይ በተፃፈው መሠረት መሥዋዕተ ኦሪቱን አሳልፎ አዲስ ቃል ኪዳን ያደረገበት ስለሆነ፣ የብሉይ በበጎች፣ በጊደሮች ደም የተመሠረተ ሲሆን አዲስ ኪዳን ግን ሰዎችን በሚያድን በክርስቶስ ደም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ ከብሉይ ኪዳን ቀጥሎ የመጣ ስለሆነ ነው:: ራሱ ጌታችን ዘመኑን አድሶ፣ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ተመላልሶ ያስተማረው ትምህርት የሠራልን ሥርዓት የሰጠንም ኪዳን ነው:: ከዚያ ከእርሱ ልደት ጀምሮ ወደዚህ ያለውን ዘመን ሐዲስ ይለዋል:: ስለዚህ በዚህ በአዲሱ ዘመን የተፃፉት ቅዱሳት መጻሕፍት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ::

### የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአራት ይመደባሉ:: ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ነው::

**ሀ. የኦሪት /ሕግ መጻሕፍት/አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት**
1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት

3. አሪት ዘሌዋውያን
4. አሪት ዘኁልቊ
5. አሪት ዘዳግም

## ለ. የታሪክ መጻሕፍት

6. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል
10. 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት
11. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
12. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ /ጸሎተ ምናሴን/ ይጨምራል
13. መጽሐፈ ዕዝራ እና መጽሐፈ ነህምያ
14. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል እና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ
15. መጽሐፈ ጦቢት
16. መጽሐፈ ዮዲት
17. መጽሐፈ አስቴር
18. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
19. 2ኛ እና 3ኛ መቃብያን
20. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን
21. መጽሐፈ ኩፋሌ
22. መጽሐፈ ሄኖክ

## ሐ. የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት

23. መጽሐፈ ኢዮብ
24. መዝሙረ ዳዊት
25. መጽሐፈ ምሳሌ
26. መጽሐፈ ተግሳጽ
27. መጽሐፈ መክብብ
28. መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን
29. መጽሐፈ ጥበብ
30. መጽሐፈ ሲራክ

## መ. የነቢያት መጻሕፍት

31. ትንቢተ ኢሳይያስ
32. ኤርምያስ/ሰቆቃወ ኤርምያስ፣ተረፈ ኤርምያስ፣ባሮክ/
33. ትንቢተ ሕዝቅኤል
34. ትንቢተ ዳንኤል/ ሶስና፣ ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል/
35. ትንቢተ ሆሴዕ
36. ትንቢተ አሞጽ
37. ትንቢተ ሚክያስ
38. ትንቢተ ኢዩኤል
39. ትንቢተ አብድዩ
40. ትንቢተ ዮናስ
41. ትንቢተ ናሆም
42. ትንቢተዕንባቆም
43. ትንቢተ ሶፎንያስ
44. ትንቢተ ሐጌ
45. ትንቢተ ዘካርያስ
46. ትንቢተ ሚልክያስ

## የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈልና ዝርዝር

## ሐዲስ ኪዳን በ5 ክፍሎች ይከፈላል።

**ሀ. የሕግ/የወንጌል/ የምሥራች ክፍል**

1. የማቴዎስ ወንጌል
2. የማርቆስ ወንጌል
3. የሉቃስ ወንጌል
4. የዮሐንስ ወንጌል

**ለ. የታሪክ ክፍል**

5. የሐዋርያት ሥራ

**ሐ. የመልእክት ክፍል**

6. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች
7. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች መጀመሪያ
8. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ሁለተኛ
9. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች
10. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ
12. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ
13. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ መጀመሪያ
14. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሁለተኛ
15. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ መጀመሪያ
16. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ ሁለተኛ
17. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ
18. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና
19. የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን
20. የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት መጀመሪያ
21. የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ሁለተኛ
22. የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት መጀመሪያ
23. የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ሁለተኛ
24. የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት ሦስተኛ
25. የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት
26. የቅዱስ ይሁዳ/የያዕቆብ ወንድም/ መልእክት

**መ. የትንቢት ክፍል**

27. የዮሐንስ ራእይ

**ሠ. የሥርዓት መጻሕፍት**

28. መጽሐፈ ትእዛዝ
29. መጽሐፈ ግጽው
30. መጽሐፈ አብጥሊስ
31. መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን
32. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
33. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ
34. መጽሐፈ ዲድስቅልያ
35. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

በጠቅላላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ናቸው። ከእነዚህም መካከል ሌሎች አካላት ያልተቀበሏቸው ቅዱሳት መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ኩፋሌ
2. መጽሐፈ ሄኖክ
3. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣
መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ
4. መጽሐፈ ጥበብ
5. መጽሐፈ ጦቢት
6. መጽሐፈ ዮዲት
7. መጻሐፈ ሲራክ
8.መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
9. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ፣
መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ
10. መጽሐፈ ምናሴ/2ኛ ዜና መዋዕል ጋር አንድ ሆኖ የሚቆጠር ነው።/
11. መጽሐፈ ባሮክ፣ ተረፈ ኤርምያስ ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ እና /ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር አንድ ሆኖ የሚቆጠር ነው/
12. ተረፈ ዳንኤል፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ሶስና /ከትንቢተ ዳንኤል ጋር አንድ ሆኖ የሚቆጠር ነው/
13. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን
14. መጽሐፈ ትእዛዝ
15. መጽሐፈ ግፅው
16. መጽሐፈ አብጥሊስ
17. መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን
18. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ
19. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ
20. መጽሐፈ ዲድስቅልያ
21. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

# 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ጥናት

## ብሉይ ኪዳን

### የሕግ መጻሕፍት

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኁልቁ
5. ኦሪት ዘዳግም

### የታሪክ መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ
2. መጽሐፈ መሳፍንት
3. መጽሐፈ ሩት
4. 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል
5. 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት
6. 1ኛ ዜና መዋዕል
7. 2ኛ ዜና መዋዕል
- ጸሎተ ምናሴ
8. መጽሐፈ ኩፋሌ
9. መጽሐፈ ሄኖክ
10. መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ
11. ዕዝራ ካልዕና ዕዝራ ሱቱኤል
12. መጽሐፈ ጦቢት
13. መጽሐፈ ዮዲት
14. መጽሐፈ አስቴር
15. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
16. መጽሐፈ ዳግማዊና ሣልሳዊ መቃብያን
17. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን

### የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት

1. መጽሐፈ ኢዮብ
2. መዝሙረ ዳዊት
3. መጽሐፈ ምሳሌ
4. መጽሐፈ ተግሣጽ
5. መጽሐፈ መክብብ
6. መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን
7. መጽሐፈ ጥበብ
8. መጽሐፈ ሲራክ

### የትንቢት መጻሕፍት

1. ትንቢተ ኢሳይያስ
2. ትንቢተ ኤርምያስ
   - ሰቆቃወ ኤርምያስ
   - ተረፈ ኤርምያስ
   - ባሮክ
3. ትንቢተ ሕዝቅኤል
4. ትንቢተ ዳንኤል
   - ሶስና
   - ተረፈ ዳንኤል
   - ጸሎተ ሠለስቱ ደቂቅ
5. ትንቢተ ሆሴዕ
6. ትንቢተ አሞጽ
7. ትንቢተ ሚክያስ
8. ትንቢተ ኢዩኤል
9. ትንቢተ አብድዩ
10. ትንቢተ ዮናስ
11. ትንቢተ ናሆም
12. ትንቢተ ዕንባቆም
13. ትንቢተ ሶፎንያስ
14. ትንቢተ ሐጌ
15. ትንቢተ ዘካርያስ
16. ትንቢተ ሚልክያስ

# የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና ጸሐፊዎቻቸው

| መጻሕፍት | ጸሐፍት | መጻሕፍት | ጸሐፍት | መጻሕፍት | ጸሐፍት |
|---|---|---|---|---|---|
| 5ቱ የሕግ መጻሕፍት<br>ዘፍጥረት<br>ዘጸአት<br>ዘሌዋውያን<br>ዘኁልቁ<br>ዘዳግም | ሙሴ | መጽሐፈ ጦቢት | - | ትንቢተ ኢሳይያስ | ኢሳይያስ |
| መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ | ኢያሱ | መጽሐፈ ዮዲት | - | ትንቢተ ኤርምያስ | ኤርምያስ |
| መጽሐፈ መሳፍንት | ሳሙኤል | መጽሐፈ አስቴር | መርዶክዮስ | ትንቢተ ሕዝቅኤል | ሕዝቅኤል |
| መጽሐፈ ሩት | ሳሙኤል | መጽሐፈ መቃብያንቀዳማዊ | መቃብያን | ትንቢተ ዳንኤል | ዳንኤል |
| መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ | ሳሙኤል | መጽሐፈ መቃብያንካልዕና ሣልስ | መቃብያን | ትንቢተ ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ | - | መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን | ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን | ትንቢተ አሞጽ | አሞጽ |
| መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና ካልዕ | ሳሙኤል | መጽሐፈ ኢዮብ | ኢዮብ | ትንቢተ ሚክያስ | ሚክያስ |
| መጽሐፈ ኩፋሌ | ሙሴ | መዝሙረ ዳዊት | ዳዊት | ትንቢተ ኢዩኤል | ኢዩኤል |
| መጽሐፈ ሄኖክ | ሄኖክ | መጽሐፈ ምሳሌ | ሰሎሞን | ትንቢተ አብድዩ | አብድዩ |
| መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ | ነህምያ | መኃልየ መኃልይ | ሰሎሞን | ትንቢተ ዮናስ | ዮናስ |
| መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤልና ዕዝራ ካልዕ | ዕዝራ | መጽሐፈ ተግሣፅ | ሰሎሞን | ትንቢተ ናሆም | ናሆም |
| | | መጽሐፈ ጥበብ | ሰሎሞን | ትንቢተ ዕንባቆም | ዕንባቆም |
| | | መጽሐፈ መክብብ | ሰሎሞን | ትንቢተ ሶፎንያስ | ሶፎንያስ |
| | | | | ትንቢተ ሐጌ | ሐጌ |
| | | | | ትንቢተ ዘካርያስ | ዘካርያስ |
| | | | | ትንቢተ ሚልክያስ | ሚልክያስ |

# የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ጥናት




# የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትና ጸሐፊዎቻቸው

| መጻሕፍት | ጸሐፍት |
|---|---|
| የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል | ወንጌላዊው ማቴዎስ |
| የቅዱስ ማርቆስወንጌል | ወንጌላዊው ማርቆስ |
| የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል | ወንጌላዊው ሉቃስ |
| የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል | ወንጌላዊው/ሐዋርያው/ ዮሐንስ |
| የሐዋርያት ሥራ | ወንጌላዊው ሉቃስ |
| የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት | ቅዱስ ጳውሎስ |
| የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክታት | ሐዋርያው ጴጥሮስ |
| የቅዱስ ዮሐንስ መልእክታት | ወንጌላዊው/ሐዋርያው/ ዮሐንስ |
| የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት | ሐዋርያው ያዕቆብ |
| የቅዱስ ይሁዳ መልእክት | ሐዋርያው ይሁዳ |
| መጽሐፈ ራእየ ዮሐንስ | ወንጌላዊው/ሐዋርያው/ ዮሐንስ |
| መጽሐፈ ትእዛዝ | ቅዱሳን ሐዋርያት |

| | |
|---|---|
| መጽሐፈ ግጽው | |
| መጽሐፈ አብጥሊስ | |
| መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን | |
| መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ | |
| መጽሐፈ ዲድስቅልያ | |
| መጽሐፈ ቀሌምንጦስ | ቅዱስ ቀሌምንጦስ/ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር/ |

## ሌሎች እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት የማይቀበሉት ለምንድን ነው?

ብዙዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ቅዱሳት መጻሕፍት ላለመቀበል የሚያነሷቸው ጥያቄዎች አሉ:: ***ለምሳሌ*** አንዳንዶች በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በማስረጃነት ደረጃ የተጠቀሰ ጥቅስ የለም ይላሉ:: ይህ አባባላቸው የሐዲስ ኪዳንን መጻሕፍትን በደንብ ካለማንበብ የተነሣ እንጂ በብዙ ቦታዎች እንደተጠቀሱ ማስረጃዎችን ከብሉይ ኪዳንም ከሐዲስ ኪዳንም እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል::

***ለምሳሌ*** የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በቁጥር 14 ላይ «ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስለጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ::» በማለት የሄኖክን ትንቢት ጠቅሶ ጽፏል:: ይህም በመጽሐፈ ሄኖክ.1.9 ላይ ይገኛል::

ወንጌላዊው ማቴዎስም በመጽሐፉ ነቢዩ ኤርምያስን ጠቅሶ «በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለውጠ ከእስራኤል ልጆችን አንዳንዶቹ የገመቱትን የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት የሚል ተፈፀመ::» በማለት ጽፏል:: ማቴዎስ ነቢዩ ኤርምያስን ጠቅሶ የፃፈው በ66ቱ የትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ የለም:: ነገር ግን መናፍቃን አንቀበልም ከሚሉት መጽሐፍ ከተረፈ ኤርምያስ 7.5 ላይ ይገኛል::

በመጽሐፈ መቃብያን ወንድሞቹ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ተሰብስበው የወሰኑት በየዓመቱ መከበር ያለበት የመታደስ በዓል ከመጽሐፈ መቃብያን በቀር ሌሎች የብሉያት መጻሕፍት ላይ አልተጠቀሰም:: ነገር ግን ዮሐንስ በወንጌሉ.10.22 ላይ ይህንን በዓል ጠቅሶት መገኘቱና ሌሎች ማስረጃዎች የመጻሕፍቱን ቅድስና ያረጋግ ጡልናል::

በተጨማሪም ተከራካሪዎች ካስወጧቸው የብሉያት መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች አሉ:: ለምሳሌ-

ጦቢ.ት.4.16 እና ማቴ.7.12
ጦቢ.ት.4.7-10 እና ማቴ.6.19-20
ዮዲ.ት.8.12 እና ማቴ.4.7

በመሠረቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የግድ በሐዲስ ኪዳን መጠቀስ አለባቸው የሚል የሃይማኖት ድንጋጌ የለም:: እንዲህ ቢሆን ኖሮ ***ለምሳሌ*** ከመጽሐፈ አስቴር፣ ከመጽሐፈ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሰ የለምና ተቀባይነት የሌላቸው መጻሕፍት ናቸው በተባሉ ነበር::

ስለዚህ ከአጠቃላይ መናፍቃን መጻሕፍትን በጥንቃቄ ካለማንበብ የተነሣ በሐዲስ ኪዳን አልተጠቀሱም ለሚሉት እነዚያ ካልተቀበሏቸው መጻሕፍት በሐዲስ ኪዳን እንደተጠቀሱ ተገንዝበናል:: እነዚህን መጻሕፍት የተቀበልናቸው በሐዲስ ኪዳን ስለተጠቀሱም ስላልተጠቀሱም አይደለም:: ነገር ግን እውነተኛነታቸውን በማረጋገጥ ነው::

**/ይቆየን/**
ወስብሐት ለእግዚአብሔር